Institute of Development & Education for Africa, Inc.

1199 Whitney Ave Suite 523 Hamden, Ct 06517 Tel: 203-789-1990 or 203-747-2763
webmaster@africanidea.org

ነሐሴ 13 2005 ዓ.ም. August 19 2013

# የአሲምባ ፍቅር

## ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ነፃነትና ዲሞክራሲ በተደረገ ህዝባዊ ትግል ላይ የተመሰረተ እውነተኛ ታሪክ

## ካሕሳይ አብርሃ ብስራት
አዲስ አበባ 2005 ዓ.ም.

### አቃቂር፡ ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር

የዛሬ ሁለት ዓመት ማለትም በ 2005 ዓ.ም. አስማማው ኃይሉ ስለ ኢሕአሠ ለጻፈው መጽሓፍ አቃቂር ስጽፍ እንዲህ ብዬ ነበር፡ "ይህ መጽሓፍ ኢሕአሠ ለነበሩ ጓዶች ትዝታ፣ ለተሰዉት ደግሞ ሓወልትና ወመዘክር ነው። ይህ የታሪክ ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ስላለበት በኢሕአፓ/ሠ ዙርያ ተሰማርተው የነበሩትን አሁን በሂወት የሚገኙ ጓዶች ለአሁንና ለመጪው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ቅርሱን ማውረስ ግዴታቸው መሆን አለበት የሚል እምነት አለኝ።" (www.africanidea.org/Yethiopia_hizbawi_aboye_Serawit.pdf)

በተመሳሳይ መልክ አሁን ካሕሳይ አብርሃ ታሪካዊ ሓለፊነት በመቀበል *የአሲምባ ፍቅር* የተሰኘውን መጽሓፍ ለአንባብያን አቅርቦልናል። ደራሲው ይኸንን መጽሓፍ መታሰብያነቱ "በገጠርም ሆነ በከተማ ለሕዝብና ለሐገር ሲሉ የሕይወት መስዋእትነት ለከፈሉ የኢሕአፓ/ኢሕአሠ ሰማዕታት ይሁንልኝ" ይላል።

*የአሲምባ ፍቅር* ሁለት ዓይነት ፍቅር ያካተተ መጽሓፍ ነው። አንደኛው ደራሲው ለአሲምባ ጓዶቹና ለተሰለፈበትና በቍርጠኝነት ለመስዋእት ለተዘጋጀበት የኢሕአፓ ዓላማ ሲሆን ሁለተኛው ፍቅር ደግሞ ባሕርያዊ ግን ግላዊ ፍቅር ሆኖ ከተሰዋችው ጓዱና ፍቅረኛው "ድላይ" (ስመኝ ምንአለ) ከነበረው የፍቅር ግንኙነትና ስሜት የሚየንጸባርቅ ነው። እነዚህን ሁለት የፍቅር ቅይጦች ከሞላ ጎደል የመጽሓፉን ዋና ይዘት የሚያጠናቅሩ ሆነው ደራሲው በመቅድሙ እንዳስቀመጠው ደግሞ "በእርግጠኝነት ልናገር ከምችለው ከራሴ ታሪክ በመነሳትና የሌሎቹን በተለይም የተሰዉ ጓዶቼን ታሪክ በማካተት ለመጻፍ በቍርጠኝነት ተነሳሁ። እነሆ እውንም ሆነ" በማለት ጥርት ባለ አገላለጽ ስላስቀመጠው ለሁሉም አንባቢ የመጽሓፉ መልእክት ግልጽ ነው።

ካሕሳይ አብርሃ (አማኑኤል - የሜዳ ስሙ -) መጀመርያ ኢሕአሠ እግር ሲተክል ወደ ሠራዊቱ ከተቀላቀሉት ጓድ ሲሆን ስለ ሠራዊቱ እድገትና ግንባታ በቀጥታ መመስከርና መተረክ ስለሚችል ሓለፊነቱም ስለተሰማው ይኸንን መጽሓፍ ለመድረስ በቅቷል። ይኸንን ታሪካዊ ግዴታም በዚሁ መልክ ያስቀምጠዋል፦

“ስለአለፉት ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን መሥዋእትነትና እውነተኛ የወገን ፍቅር ስሜት፣ ቢያንስ የምናውቀውን ያህልና በምንችለው መንገድ መመስከር፣ አንዱ ሓላፊነታችን ነው። የራሳቸውን ኑሮ ጥለው፣ ለሌሎች ነጻነት ሲሉ መሥዋእትነት የከፈሉ ኢትዮጵያውያንን፣ በተቻለንና ባለን አቅም ለመዘከርና ቢያንስ ስማቸው በታሪክ መዝገብ እንዲቀመጥ ለማድረግ፣ መጣጣር ተገቢ ነው። ለሌሎችም ስለሰው ልጅ ነጻነት በነበራቸው እምነት ለተሰዉ፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ዓላማ የአካልና የአእምሮ ስቃይ ለደረሰባቸው በሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን፣ ስለተቀበሉት ስቃይና መከራ ያለንን ትልቅ ክብር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመግለጽ በማሰብ ነው ይህ መጽሐፍ የተጻፈው።”

ይህ መጽሐፍ በመሰረቱ ሦስት ዓይነት አንባብያን ሊማርክ ይችላል፦ 1) በኢሕአፓ ና ኢሕአሠ ተሰልፈው የነበሩና አሁን በህይወት ያሉት፣ 2) በኢሕአፓ ና ኢሕአሠ ያልተሳተፉ ሆኖም በወቅቱ በመኢሶን፣ በህዋሓት፣ በኦነግ፣ በኤርትራ ግንባሮች ወዘተ የተሳተፉና ሌሎች ኢትዮጵያውያን በማንኛውም ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ያልተሳተፉ፣ 3) አሁን ያለው ወጣት ኢትዮጵያዊ ትውልድ ግን ኢሕአፓና ዓሲምባን በወሬ ወይም በዝና ብቻ የሚያውቅ።

ለአንደኛው ስብስብ ወይም በኢሕአፓ ዙርያ የተፋለሙትን መጽሓፉ ሁለት ዓይነት ተቃራኒ ስሜቶችን ሊያሳድርባቸው ይችላል። ሓዘንና ሰቆቃ እንዲሁም ደስታ። በፓርቲውና በሠራዊቱ ለተሰለፉት አሁን በህይወት ያሉ ጓዶች መጽሓፉን ሲያነቡ በትዝታና በሰቀቀን መዋጣቸው አይቀርም፣ ነገር ግን መጽሓፉ ለወደቁት ጓዶች እንደሚንቀሳቀስ ሓወልት ማገልገሉን ሲረዱ ደግሞ በደስታ መፈንጨታቸው የማይቀር ነው። እኔ በበኩሌ መጽሓፉን ሳነበው ሁለት ዓይነት ስሜቶች በመፈራረቅ ከማስተናገድ አልፈው ሰውነቴና መንፈሴን ደህና አድርጋው ቀጥቅተውታል። ሆኖም ግን አቃቂር መጻፍ ስለነበረብኝ መጽሓፉን ከጫፍ እስከ ጫፍ (ከመሃሉም ትንፋሽ እያጠረብኝ) ማንበቡ የግድ ነበር።

ሁለተኛው መደብ ወይም እንደ ተቃዋሚ ኃይሎች ደርግን የወጉት ደግሞ በኢሕአፓ/ሠ የነበራቸውን አሉታዊ አስተያየት ሊያስቀይር የሚችል ሰነድ ነው መጽሓፉ። ይህ ያልኩበት ምክንያት ደግሞ “ኢሕአሠ አይዋጋም” ለሚለው አፈ-ታሪክ ወይም መሠረተ-ቢስ እምነት መጽሓፉ በሚገባ ሰለሚያፈርሰው ነው። ምክንያቱም አቶ ካሕሳይ የሠራዊቱ አጠቃለይ ውሎዎችና በትግራይ፡ በወሎ፡ በጎንደር ያካሄደውን ጦርነቶች በሚያሳምንና በፍቱንነት አጠናቅሮታል።

ሦስተኛው ኣንባቢ ማለትም ያሁኑ ወጣት የኢትዮጵያ ትወልድ ከዚህ መጽሓፍ የሚያገኘው ነገር ቢኖር እውቀትና ቅርስ ናቸው። ወጣቱ ትውልድ ኢሕአፓን ባያውቀውም ቅሉ በእንዲህ ዓይነት መጻሕፍት ግን ስለ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ማወቅ ይችላል። የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ያልኩበትም ምክንያት ኢሕአፓ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በላቀ መልኩ ኅብረ-ብሔር ለመኖሩና ከሁሉም ብሔራት የተውጣጡ አባላትም ስለነበሩት ነው።

ካሕሳይ አብርሃ ኢሕአሠን የተቀላቀለው በመስከረም ወር 1968 ዓ.ም ነው። ይኸም ማለት ገና ሠራዊቱ በእንጭጭነቱ ዘመን ማለት ነው። ደራሲውም እንደሆነ ገና በወጣትነቱና በለጋ ዕድሜው ነበር ኢሕአፓን/ኢሕአሠን የመረጠው። በዛን ጊዜ ደራሲው በትምህርት ብዙ አልገፋም ነበር፣ በአማለካከትም (በተለይም በርእዮተ ዓለማዊ አመለካከት) ጨቅላ ነበር። ነገር ግን በምዕራፍ አንድ በግልጽ እንዳስቀመጠው “ማንኛውም ሰው የሕይወት መዞርያ፣ መታጠፍያ ወይም ኩርባዎች

ይኖሩታል" ይልና "የኔ ኩርባዎች የገበሬ ቤተሰቦች፣ አሲምባ፣ ይመር ንጉሤ ና ድላይ ናቸው" ብሎ ይደመድማል።

ይመር ንጉሤ የደራሲው ባለውለታ ነው። በመጀመርያው የኢሕአሠ የወሎ እንቅስቃሴ ካሕሳይም ነበረበት፣ ግን ያለ ብቁ ጥናትና ዝግጅት የተካሄደ እንቅስቃሴ ስለነበር የደርግ ሚሊሺያና የአካባቢው ገበሬዎች በኢሕአሠ ላይ ጥቃት ስለሰነዘሩ ብዙ ጓዶች ተማረኩና ተሰዉ፣ አማኑኤልን ከኋላ ሊያጠቃው የሞከረ ገበሬ ወድያው አየውና በማነጣጠር ተኩሶ ሊገለው ሲችል ኅሊናው አልፈቅድ ብሎት ሳይገድለው ቀረ። ሁለቱም እጅ ለእጅ ተያይዘው ተጠላለፉና መሬት ላይ ዘው አሉ፣ ገበሬውም የአማኑኤልን እጆች በመያዝ በገመድ ሊያስረው ቃጣ ግን አልቻለም። በመጨረሻ ግን በሁለቱም ዘንድ የመግባባት መንፈስ አንዣበበና ገበሬው "ለምን ግን አነጣጥረህ ስታበቃ አልገደልከኝም" ብሎ አማኑኤልን ጠየቀው፣ አማኑኤል ደግሞ "እኔ አንተን ብገድል ልጆችህና ሚስትህ ይሰቃያሉ፣ አንተ እኔን ብትገድለኝ ግን ልጅ የለኝ ሚስት የለኝ ብሞትም ምንም አይደል" አለው።

አማኑኤል ገበሬውን በኃይለ-ቃልና በውይይት አቸነፈው፣ ገበሬውም የአማኑኤል የስነ-ልነቦና ምርኮኛ ሆነ። ይህ ሁሉ የተካሄደበት ቦታ ወሎ ሮቢት አጠገብ ሆኖ የገበሬው ስም ደግሞ ይመር ንጉሤ ይባላል። በአከባቢው ግን ይመር ንጉሤ አንድ የኢሕአፓ ታጋይ ማርኳል ብሎ ስለተወራ የደርግ ሰዎች ይመር ቤት ድረስ መጥተው "የማረክኸው ሰው የት አለ" ብለው ጠየቁትና "ገድየዋለሁ" ብሎ ድርቅ አለ። አማኑኤልን ግን ከቤቱ አቅራብያ ከነበረው ጎጆ ነበር የደበቀው። ከዛ ኋላ በፍጥነት አማኑኤልን ጸጉሩን ተላጭቶ ቅቤ እንዲቀባና አገልድም እንዲለብስ ካደረገ በኋላ በጠዋቱ ወደ አውቶቡስ ተራ ወስዶ ሊሰኘው ሲል መንገድ ላይ ሌሎች ሰዎች ያዩዋቸውና "ይህ የማረክኸው ሰው ነው?" ብለው ይመርን ይጠይቁታል፣ "የማረክኹት ሰው'ማ ገድየዋለሁ፣ ይኽ እረኛየ ነው" አላቸው። ታጋዩ አማኑኤል ባላሰበው መንገድና አጋጣሚ ወደ አሲምባ ተመልሶ ከጓዶቹ ጋር ተቀላቀለ። ከሰላሳ ዓመት በኋላ ግን ካሕሳይ መካ ወይም ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ተሳለሚ ውሎታውን ለመክፈል ወደ ወሎ ሮቢት ዘለቀ፣ ይመር ከሞተ ቆይተዋል፣ ልጆቹንና ሚስቱን ግን አገኛቸው። መሰንበት ደግ ነው ብዙ ነገር የሳያል!

ኢሕአሠ የተፈጠረበትን ሠፈር ዓዲ ኢሮብን አስመልክቶ ደራሲው በትክክለኛ መንገድ ገልጸታል፦ "የዓዲ ኢሮብ ሕዝብ የመቻቻል፡ የእንግዳ ተቀባይነትና የሕዝብና ታጋይ አንድነት ፍቱን አርአያ ነው። ዓዲ ኢሮብ በትግራይ ክፍለሃገር ሰሜን ምስራቅ በዓጋመ አውራጃ፣ አዲግራት ከተማ በስተምስራቅ የሚገኝ፣ በአብዛኛው ተራራማ የሆነ ወረዳ ነው።…የዓዲ ኢሮብ፡ ደብረመላና የሃዶ ኗሪዎች ወንዱና ሴቱን እንዲሁም ህፃናቱን የሚያሳትፍ ማኅበራዊ ኑሮ አላቸው። እንደ ዴጋ ክርስትያኑ አክራሪነት አይታይባቸውም…ዓዲ ኢሮብ የተለያዩ ሃገራዊና ታሪካዊ የኃይማኖት ቅርሶች ያሉት ወረዳ ነው…የኢሮብ ሕዝብ ውግያ የማይፈራ፣ ያገኘውን ተካፍሎ የሚበላ፣ ያመነውን በፍጹም አሳልፎ የማይሰጥ፣ እስከ ተፈለገው ጊዜ ደብቆና ጠብቆ የሚያቆይ ሕዝብ ነው። የኢሮብ ሕዝብ ካመነ አመነ ነው።"

ደራሲው ስለ ዓዲ ኢሮብ ያደረገውን ገለጻ ሙሉ በሙሉ የምስማማበት ነው፣ ምናልባት አከራካሪ ሊሆን የሚችለው "ኢሮብ የሚለው ቃል ኢሮባ ከሚለው ሲሆን ይህም በሳሆ ቋንቋ ወደ ቤት ግባ ማለት ነው" የሚለውን ነው። ደራሲው ከአፈ-ታሪክ ያገኘውን ትርጉም ትክክል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እኔ በበኩሌ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ጥናት አድርጌ ነበረና 'ኢሮብ' 'ምዕራብ' ከሚላው ቃል የመጣ ሳይሆን አይቀርም። ዓዲ ኢሮብ በትግራይ በስተምስራቅ የሚገኝ ወረዳ ቢሆንም ከኣፋር ወይም ቀይ ባሕር አዋሳኝ አንጻር ካየነው ግን የፀሓይ ግባት ወይም ምዕራብ ነው

የሚሆነው። በተጨማሪ ‘ምዕራብ’ የሚለውን የኢትዮጵያ ሴማዊ ቃል ከሌሎች ከኢትዮጵያ ውጪ ካሉት ሴማዊ ቃላት ጋር የሚገጥም ነው። ለምሳሌ በጥንታዊት መሶጶታምያ (አሁን ኢራቅ) ኣቃድያን የተባሉ ነገድ የፀሓይ ግባትን ‘አራቡ’ ይሉት ነበር፣ በኡጋርቲክ ደግሞ የፀሓይ ጥልቀትን የሚገልጽ ግሥ ‘አራቡ’ ነው፣ በፎኒሽያን (ከእብራይስጥ ቋንቋ የተዛመደ ቋንቋ) ‘ኣሮብ’ ማለት ምዕራብ ማለት ነው። የግሪኩ ቃል ‘ኢሮፕ’ (አሁን የአውሮጳ አህጉር ስም የሆነውን) ‘ኢረብ’ ከሚል ሴማዊ ቃል ነው የፈለቀው። ስለሆነም ‘አውሮጳ’ የሚል ቃል የፈለቀው ከሴማዊ ቋንቋ ስለሆነ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ‘ኢሮብ’ ከ ‘አውሮፓ’ የመነጨ ሳይሆን ‘አውሮፓ’ ከ ‘ኢሮብ’ የፈለቀ መሆኑን ከላይ ያስቀመጥኩትን ርቱዕነት በሚገባ ያሳያል።

በምዕራፍ ሁለት ደራሲው የመጀመርያ የኢሕአሠ የዳሎል እንቅስቃሴ (ኦፐረሽን) ስኬታማ እንደ ነበር ይገልጽና እዛውም “በርካታ ንብረት አግኝተናል፣ እነዚህም ማስ ጠበንጃዎች፣ የሕክምና መድኃኒቶች፣ የግልኮስ እሽጎችና በጥሬ ገንዘብ አስራ ስድስት ሺህ ብር ነበሩ” ይላል።

በዚሁ ምዕራፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መርሆ የነበወረውን “መሬት ላራሹ” ኢህአሠ በደብረ ዳሞ አከባቢ በግብር እንደተረጎመው ጸሓፊው ይገልጻል። መሬቱ ግን ዝም ብሎ በዘፈቀደ ኣይደለም ለሕዝቡ የተሸነሸነውና የታደለው። የመሬት ጉዳይ “የሚያስፈጽም የገበሬ ማኅበር ሸንጎ እንድያደርጉ፣ ሊቀ መንበር እንዲመርጡና በጋራ ወስነው መሬት እንዲከፋፈሉ” የአከባቢው ሕዝብ ከተነገራቸው በኋላ መሬቱ ታደለ። ግን ውድያውኑ ወሬው በየቦታው ተዳረሰና ዓሲምባ አከባቢ ያለውም ሕዝብ መሬትን አስመልክቶ ተመሳሳይ መፍትሔ እንድያገኝ ጠየቀ። ሠራዊቱም የሕዝቡን ጥያቄ በይበልጥ ለማሟላት “የብዙኃን ድርጅቶችን ማቋቋም” ጀመረ።

ምዕራፍ ሦስት ስለ ‘ወልድያ ደርሶ መልስ’ ሆኖ፣ ጠቅላላ የሠራዊቱ ጉዞ ከዓሲምባ እስከ ቀለም፡ እስከ ወሎ ሮቢት እንደገና ወደ ዓሲምባ ማለትም ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ያልተሳካ የኢሕአሠ ኦፐረሽን ደራሲው በሰፊው ዘርዝሮታል። ለምዕራፍ ሦስት የስነ-ጽሑፍ ድምቀት የሰጠው ደግሞ የኢሕአሠ መዝሙርና “የጀግና ሰው መልኩ” አጭር ግጥም ናቸው። ደራሲው በዚሁ መልክ ያቀርባቸዋል፦

ቢሰበር አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ
ላዲስ ስርዓት ልምላሜ
ፍፁም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ህይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በወደቁት ጀግኖች ፋና

የኢሕአሠ መዝሙር (ገጽ 124)

ከወሎ ሮቢት ወደ ዓሲምባ ጉዞ ለመግለጽ ያህል ደግሞ ደራሲው በኣጭር ዘይቤ ይጀምራል፦

የጀግና ሰው መልኩ ሁለት ብቻ ነው፣
አንድ ፊት መሥዋእት በአንድ ፊት ድሉ ነው፣
የሁሉም ማሰርያ ማተቡ ነው። (ገጽ 140)

የመጀመርያ የኢሕአሠ የወሎ ጉዞ ምን ያህል ጉዳት ለሠራዊቱ እንዳደረሰ በዚሁ ምዕራፍ ተገልጿል። በዚሁ ወቅት ወሎ ውስጥ ከተማረኩት የኢሕአሠ 23 ኣባላት (ከጠቅላለው 54 ወደ ወሎ የተጓዙት) በኋላ አረመኔው ደርግ ረሸኗቸዋል። ኢሕአሠ

ገና በእንጭጭነቱ ምርጥ ምርጥ የሠራዊቱ አባላትን አጠፋ። ጥፋቱም ከአመራር ጉድለት መሆኑን፣ እኔም የምስማማበት፣ ደራሲው እንደሚከተለው አቅርቦታል፦

"እንኳንስ ጥናታዊ ውጤት ልናገኝ የወሎ ተልእኮ ከዝያ ወዲህ ተነሥቶ አያውቅም፣ እንደተከደነ ቀረ። ምናልባት አመራሩ የችግሩ ምንጭ ራሱ ጋ መሆኑን አውቆ ይሆናል፣ እውነቱን አውጥቶ ስሕተቱን በአደባባይ ለመቀበል አባላት በአመራሩ ላይ ያላቸውን እምነት እንደሚቀንስ ታስቦ ሊሆን ይችላል። በአመራር እምነት ከሌለ ደግሞ በትንሹም በትልቁም ነገር ማንገራገር ያስከትል ይሆናል። ይህ ሁሉ ከግምት ያለፈ አይደለም፣ ነገር ግን ምንም ይሁን ምን ሁኔታውን ያስከተለውን መንፈሳዊ ጉዳት ከመባባስ አላዳነውም። በተለይም ከወሎ ተልእኮ በሕይወት የተረፍነው አባላት ከጠባሳው ጋር አብረን እንድንኖር ሆነናል።" (ገጽ 169)

ምዕራፍ አራት ስለ 'ክፍለ ሕዝብ' ወይም ሕዝብን የመቀስቀስና የማደራጀት ሆኖ ይኸንን አስመልክቶ ደራሲው የኢሕአሠ ኃይል አምስት ወደ ደብረ ዳሞ እንደተጓዘችና የአቡነ አረጋዊ ዓመተ በዓልን አጋጣሚ በመጠቀም ደግሞ ሕዝብን ለመቀስቀስ ተልእኮ እነደነበራት ገልጾታል። ከዛም አልፎ ተርፎ አማኑኤልና የኃይልዋ የፖለቲካ ኮሚሳር ናደው (ኣባይ ኣብርሃ) ወደ ኮረብታማው ገዳም እንደወጡ ተገልጿል። ገዳሙ ላይ እንደደረሱ እንዳጋጣሚ የወያኔ መሪ የሆነውን አረጋዊ በርሀ ነበረና ናደው አማኑኤልን ጮህ ብሎ በመጥራት "ከኋላህ ያለው አረጋዊ በርሀ የሚባለው ቀጣፊ ነው እንዳይጠጋህ ተጠንቀቅ" አለው፣ አረጋዊም "ብጻይ (በትግርኛ ጓድ ማለት ነው) ተው እንጂ አትሳደብ ነውር ነው" አለው። ናደውም መለሰና "አንተ አጭበርባሪ ሌባ፣ የትግራይን ሕዝብ እያደናገርክ መኖር የለመድክ! ለምንድነው፣ ሐቀኛ ለመምሰል የምትሞክረው-እ? በትግራይ ሕዝብ ስም ለመነገድና ለማጭበርበር ነው?። ደግሞ ገበሬ ለመምሰል ነጠላ ደርበህ፣ ንጹህ ሰው ይመስል፣ በሕዝብ መካከል ታቦት አጅበህ ትዞራለህ፡ ሌባ! አሁንም ደጋግሜ ልክ ልክህን እነግረሃለሁ። ቀጣፊ፣ አስመሳይ ሌባ!!" እያለ እየደጋገመ ሰደበው።" (ገጽ 180)። ምናልባት በወቅቱ ካሕሳይ ያላወቀው ቢኖር፣ አባይ አብርሃና አረጋዊ በርሀ ከአንድ የትግራይ አከባቢ ስለሚመጡ ትውውቃቸው የቆየ ሊሆን ይችላል። ሌላው አማኑኤል ያልጠቀሰው ናደው ወደ ጎንደር ከተዛወረ በኋላ ብዙ አልቆየም፣ ጌታቸው ከሚባል ጓድ (የጦር ሠራዊት አባል የነበረ) አብረው ሲሄዱ ገበሬዎች ወይም የደርግ ሚሊሻዎች ተኵሰው ገደሏቸውና ተሰዉ።

በዚሁም ምዕራፍ ደራሲው ኃይል ሦስት ወደ ጎንደር በመሄድ እዛው ለሚገኘው የኢሕአሠ ሠራዊት መትረየስ ለማቀበልና ለማጠናከር ግዳጅ እንደተሰጣት ያትትና፣ ኃይልዋ እግረ መንገድዋን ከህዋሓት አባላት ውይይት አድርጋ እንደነበር ይገልጻል፦ "በውይይቱ ከሌሎችም ከኛም ጋንታዎች የፖለቲካ ብስለትና የንግግር ችሎታ ያላቸው አባላት እንዲካፈሉ ተደርገዋል። በውይይቱ የተካፈሉት አስር ያህል ሲሆኑ የሁለቱ ጋንታዎች የፖለቲካ ሐላፊዎች ኪዳኔና ገላውዲዮስም ተካፍለዋል። እኔ ጸጥታውን የመቆጣጠር ሓላፊነት ስለነበረብኝ ወጣ ገባ እያልኩ ወደ ዋርድያ መቆምያ ቦታ ደረስ መለስ እያልኩ ነበር በውይይቱ ላይ የሚሰጡት ሐሳቦችን የምሰማው።" (ገጽ 188-89) እንዲህ ዓይነት ውይይቶች ከወያኔ አባላት ጋር ብዙ ጊዜ ተካሂደዋል፣ የዝችኛዋ ውይይት ግን ትዝታው የለኝም።

በዚሁ ምዕራፍ የተጠቀሰውና አሳሳቢ ሆኖ ያገኘሁት የሠራዊቱ አባላት ወሎ የተደረገውን ስሕተት እንዳይደገም ለኣመራሩ ለማሳመን ቢሞክሩና "ተልእኮው ቢሰረዝ ይሻላል" ቢሉም አመራሩ (ኃይለ ቀጭኑና ጌዴዎን) ግን ኣሻፈረኝ ማለታቸውን ነው። "በምንም መንገድ ተልእኮው እንዳይሰረዝ አስረዱ"። በመጨረሻ ግን ዓሲምባ ከነበረው ጠቅላይ አመራር የጎንደርን አርባያ ኦፐረሽን አስመልክቶ እነ

ኃይሉ ቀጭኑን መቅጣት ሰለነበረበት "ኃይለ ቀጭኑ ለአንድ ዓመት ትጥቅ እንድያወርድ፣ በማንኛውም የፓርቲና የሠራዊት ሓላፊነት ቦታ እንዳይመደብና የመምረጥና የመመረጥ መብቱን እንዲገፈፍ" ተደረገ።

ምዕራፍ አምስት ስለ ኃይል አምስት መቶ አመሠራረትና የጎዕቶሎ የሠራዊት ቅየጣ ነው የሚያትተው። በዚሁ አዲሱ ምድብ አጋጣሚ ሆኖ አማኑኤል በኃይል ሦስት አብራው ከነበረችው ጓዲት ድላይ ጋር አብረው ኃይል አምስት መቶ ውስጥ ተመደቡ፣ የሁለቱም ፍቅር መልህቅ የተጣለውም በዚሁ ጊዜ ነው። በዚሁ ምዕራፍ ላይ ደራሲው ስለ ታሪካዊት የጥንት ከተማ ሓውዜን ገለጻ ካደረገ በኋላ ስለ ኤዛና ሴዛና ወይም ስለ አብርሃና አጽብሃ ወንድማማች የአክሱም ነገሥት ያወራል። ነገር ግን ክርስትያን ከሆኑ በኋላ "ስማቸው ተቀይሮ ኤዛናና ሴዛና ተባሉ" ያለውን የተገላቢጦሽ አቀማመጥ ነው። ኤዛና የቅድመ-ክርስትያን ስም ነው፣ አብርሃ ደግሞ የክርስትያን ስም። ነገር ግን ኤዛና 'አብርሃ' የሚለውን የክርስትያን ስም ቢሰጠውም በታሪክ ሰነዶች በኤዛና ነበር የሚታወቀው። በነገራችን ላይ ኤዛና ሌላም አደፋ የሚባል ወንድም ደግሞ ነበረው። ወደ ኩሽ (መርወ፣ አሁን ሰሜን ሱዳን) የተንቀሳቀሰውን የኢትዮጵያ ሠራዊት የመሩት አደፋና ሴዛና ነበሩ። የአክሱም ዘመነ መንግሥት ካበቃ በኋላ የዛጌ ስርወ-መንግሥት በላስታ አከባቢ ተቋቋመና የአዲሱ ሥርዓት ከተማ አደፋ ሆነች፣ ቀጥሎም ሮሃ (አሁን ላሊበላ) ዋና ከተማና መናኸርያ ሆና ነበር።

በዚሁም ምዕራፍ ከፍተኛ ቦታ የያዘችው ድላይ ናት፣ መጽሓፉም በከፊሉም ቢሆን ስለስዋና ከአማኑኤል ጋር የነበራት ግንኙነት ነው ቢባል ማጋነን ኣይሆንም። ነገር ግን ደራሲው ስለ ሁለቱ ፍቅር በተናጠል ሳይሆን ከኣጠቃላይ የትግሉ ሂደት፣ የሠራዊቱ እንቅስቃሴና የግጥምያ ጥሪ እንዲሁም ተልእኮ እያቆራኘ ነው የጻፈው።

በዚሁ ምዕራፍ ደራሲው በፓርቲው የተከሰተውን "የመከፋፈል ምልክቶች" ና "ብርሃነ መስቀል ከፓርቲው እንደተገለለ" ከጠቀሰ በኋላ " 'ሀ' ና 'ለ' የሚባሉ ስማቸው ያልተጠቀሱ የፓርቲ አባላት አንጃ በመፍጠራቸው ምክንያት ከድርጅቱ የተባረሩት መሆኑን ተገለጸ" ይላል። ለነገሩ፣ በኋላም እንደታወቀው 'ሀ' ና 'ለ' ብርሃነመስቀልና ጌታቸው ማሩ ናቸው። አሁን በቅርቡ የጌታቸው ማሩ "ሚስት" የጻፈችው መጽሓፍ (ግን ያላነበብኩት) አለና ምናልባት የማናውቀው ሚስጢር በመጽሓፉ ተመዝግቦ ሊሆን ይችላል።

ምዕራፍ ስድስት "የውቅሮ ተልእኮ" ወይም "አራት ኃይሎች በክልተ ኣውላዕሎ" ያደረጉትን ኦፐረሽን ነው የሚያትተው። አጋጣሚ ሆኖም እኔ ስለዚሁ ኦፐረሽን ለአስማማው መጽሓፍ በጻፍኩት አቃቂር ላይ ሕብስቱ "እኔ ዛሬ የምመለስ አይመስለኝም" ብሎ ነግሮኝ ነበር ያልኩትን በተመሳሳይ መልኩ ድላይ ለአማኑኤል "የምትመለሱ አይመስለኝም" ብላው እንደ ነበር ተጠቅሷል።

ምዕራፍ ሰባት ስለ "መጨረሻዎቹ ቀናት" ማለትም አማኑኤል ራሱ የፓርቲውና የሠራዊቱ መፈረካከስ ካጠና በኋላ ጠፍቶ ወደ ኤርትራ መሄዱን ነው የሚገልጸው። ግን ለአሲምባ ያለው ፍቅር ምን ጊዜም አልተቀየረም። የሚያሳዝነው ግን አማኑኤል ሱዳን ከደረሰ በኋላ መርዶ ተነገረው፣ ጓዱና ፍቅረኛው ድላይ በለሳ ላይ እንደተሰዋች አወቀ! አለቀ! እንደማንኛውም ስደተኛ ከሱዳን ፖርቶሪኮ ከዛም ቨርጂንያ ቀጥሎም ደንቨር ኮሎራዶ ገብቶ ኑሮዉን ገፋ። የዛሬ አስራ አንድ ዓመት እኔ ለሽርሽር ወደ ደንቨር ሄድኩና ከካሕሳይ አብርሃ ጋር ተገናኘን፣ እቤቱ ድረስም ሄድንና አስተናገደኝ፣ ከደንቨር ወጣ ብሎ የሚገኘውን ከፍተኛ ተራራም ላይ አብረን ወጣንና "ይህ ተራራ ዓሲምባ አይመስልም" አለኝ። የዓሲምባ ፍቅር

እንዳልወጣለትም ተረዳሁኝ፣ ሰለሆነም አሁን *የዓሲምባ ፍቅር* በሚል ርእስ መጽሓፍ መድረሱን የሚያስገርመኝ ባይሆንም የኢ.ሕአፓ/ሠ ታሪክ በዝርዝር አጠናቅሮ ለአንባብያን ማቅረቡ ግን እጅጉን ላመሰግነው እፈልጋለሁ። *የዓሲምባ ፍቅር* በጥሞና መነበብ ያለበት ድንቅ መጽሓፍ ነው።

All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc. Dr. Ghelawdewos Araia can be reached via dr.garaia@africanidea.org
አስተያየትና ጥያቄ ማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ ከላይ በተጠቀሰው ኢ-መይል ወይም webmster@africanidea.org ይጠቀሙ